

የአዲስ ኪዳን ነቢያት



"የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው፤ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፤ አሠራርም ልዩ ልዩ ነው፥ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው።" (1 ቆሮንቶስ 12:4-6)

ከነቢዩ ሚልክያስ በኋላ በእግዚአብሔር ሕዝቦች መካከል የነቢይ ድምጽ ሳይሰማ 400 ዓመታት አልፈው ነበር። ከዚህ ዝምታ የተነሳ የእስራኤል ሕዝብ የብሉይ ኪዳን መጽሕፍት ተብለው የሚቆጠሩትን ለይተውና ቀኖናውን ዘግተው ነበር።



እግዚአብሔር ግን ዝምታውን በዚሁ አልቀጠለም። ጊዜው ሲደርስ ከኢየሱስ በፊት ከነቢያት ሁሉ ታላቅ የነበረውን መጥምቁ ዮሐንስን ላከ (ማቴ 11:7-9)። ከዚያን ጊዜ አንስቶ ነቢያት በድጋሚ ብቅ ማለት ጀመሩ። አዲስ ኪዳን እንዲፃፍ ከማድረግ ጋራ ሌሎችንም ሥራዎች የሰሩት እነርሱ ናቸው።

የእነዚህ የአዲስ ኪዳን ነቢያት ታላፊነት ምንድን ነበር? እነማን ነበሩ? በብሉይ ኪዳን ጊዜ እንደነበሩት በአዲሱም ኪዳን ሀሰተኛ ነቢያት ነበሩ?



- የነቢያት ታላፊነት በአዲሱ ኪዳን
- የአዲስ ኪዳን ነቢያት:
  - የተተነበየለት ነቢይ ኢየሱስ
  - ሐዋርያት እና ነቢያት
  - ሴት ነቢያት
  - የጳውሎስ ግብረ አበሮች
  - ሀሰተኛ ነቢያት

የነቢያት ኃላፊነት በአዲሱ ኪዳን

"ትንቢትን የሚናገር ግን ለማነጽና ለመምከር ለማጽናናትም ለሰው ይናገራል።" (1 ቆሮንቶስ 14:3)

በአዲስ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ ተትረፍርፎ በመፍሰሱ ትንቢት ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ ነው (ሮሜ 12:6)። በአንዳንድ ቤተክርስቲያኖች ውስጥ ብዙ ነቢያቶች ከመኖራቸው የተነሳ ለመናገር ተራቸውን መጠበቅ ያስፈልጋቸው ነበር (1 ቆሮ 14:29-31)።

እነዚያ ነቢያት የሚጫወቱት ሚና ምንድን ነበር? (ራዕይ 19:10፣ 1:1፣ ኤፌ 4:11-12፣ 1 ቆሮ 14:3፣ የሐዋ 15:32)።

ዋና ተልዕኮዋቸው ሕዝቡን ወደ ኢየሱስ መምራት ነው

ለኢየሱስ ምስክር መሆን



ወደፊት ስለሚሆኑ ክስተቶች የመጨረሻውን ዘመን ጨምሮ ይገልጡ ነበር

የወደፊቱን ማሳወቅ



የጠላትን ጥቃት መቋቋም የምትችል ጠንካራ ቤተክርስቲያንን ይገነቡ ነበር

ማነጽ



ሕዝቡ ንስሃ እንዲገባ ኃጥያትን ይገስጹ ነበር

መገሰጽ




ለማጽናናት በተለይ የኢየሱስ ወንድም ይሁዳና ሲላስ ወደ አቢያተክርሲያናቱ ይላኩ ነበር

ማጽናናት















የአዲስ ኪዳን ነቢያት

የተተነበየለት ነቢይ ኢየሱስ

"... አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፤ እርሱንም ታደምጣለህ።" (ዘዳግም 18:16)


ኢየሱስ በዘመኑ በነበሩ ሰዎች እንደ ነቢይ ይቆጠር ነበር (ማቴ 21:11፣ ማር 6:15፣ ሉቃ 7:16፣ ዮሐ 6:14)።

እርሱም በዚህ ማዕረግ እራሱን ይጠራ ነበር (ማር 6:4፣ ሉቃ 13:33)።

ኢይሱስ በሙሴና በሌሎችም ነቢያት የተተነበየለት የሚመጣው ነቢይ ወይም መሢሕ መሆኑን ጴጥሮስ እንኳን ተናግሮ ነበር (ዘዳ 18:15፣ የሐዋ 3:18-26)።

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል የሚፈጽም ብቻ ሳይሆን እርሱ እራሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው (ዮሐ 1:1)።







እርሱ እንደ ሌሎቹ ነቢያት "ብርሃን አስተላላፊ" ብቻ ሳይሆን እርሱ እራሱ ብርሃን ነው (2 ጴጥ 1:19፣ ዮሐ 1:9፣ 8:12)።

የእርሱ ሥራ ከየትኛውም ነቢይ ሥራ ያለፈ ነው። በሕይወቱ፣ በሞቱና በትንሳኤው ለሁላችንም ዘላለምን ሊያወርስ የተቻለው ኢየሱስ ብቻ ነው!!!



ሐዋርያት እና ነቢያት

"ይህም ምስጢር አሁን ለቅዱሳኑ ሐዋርያትና ነቢያት የተገለጠውን ያህል ባለፉት ዘመናት ለነበሩ ሰዎች አልተገለጠም ነበር።"
(ኤፌ 3:5)

የአዲስ ኪዳን ሐዋርያትና ነቢያት ያላቸው ተመሳሳይ ባህሪይ:

- በእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች ናቸው (ሉቃ 11:49)
- ቤተክርስቲያንን ለመምራት ሥጦታዎችን ይቀበላሉ (1ቆሮ 12:28-29፣ ኤፌ 4:11-12)
- የቤተክርስቲያን መሠረት ናቸው (ኤፌ 2:20)
- ራዕዮችን ይቀበላሉ (ኤፌ 3:5)
- በፍርድ ይደሰታሉ (ራዕይ 18:20)

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከ ሉቃስ 11:49 በስተቀር ስማቸው በአንድ ላይ ሲጠቀስ ሐዋርያት ከነቢያት ይቀድማሉ። ጴጥሮስ ሐዋርያትን ከጥንቶቹ ነቢያት ጋር እኩል አድርጎ ያቀርባቸዋል (2 ጴጥ 3:2)።



ሐዋርያት ኢየሱስ እራሱ የትንሳኤው ምስክሮች እንዲሆኑ የመረጣቸውና የሾማቸው ናቸው (የሐዋ 10:40-41)።






በአዲስ ኪዳን በስም ከተጠቀሱት ነቢያት ውስጥ ሐዋርያው በርናባስ ፣ ስምዖን፣ ሉክዮስ፣ ምናሔ፣ ሐዋርያ ጳውሎስ፣ ይሁዳ፣ ሲላስ እና አጋቦስ ይገኙበታል (የሐዋ 11:27፣ 13:1፣ 15:32፣ 19:6-7፣ 21:10)።

ሴት ነቢያት

"ለእርሱም [ወንጌላዊው ፊልጶስ] ትንቢት የሚናገሩ አራት ደናግል ሴቶች ልጆች ነበሩት።" (የሐዋርያት ሥራ 21:9)



በአዲስ ኪዳን ስሟ የተጠቀሰው ብቸኛ ነቢዪት "የኢየሩሳሌምንም ቤዛ ለሚጠባበቁ ሁሉ ስለ ሕፃኑ [ስለ ኢየሱስ] ትናገር" የነበረችው ሐና ነች (ሉቃ 2:36-38)።



የወንጌላዊው ፊልጶስም አራት ሴት ልጆች የትንቢት ሥጦታን ተቀብለው ነበር (የሐዋ 21 :8-9)።

በተጨማሪም ትንቢት ለሴትችና ወንዶች የጋራ የሆነ ሥጦታ ተደርጎ ተጠቅሷል (1 ቆሮ 11:4-5)።





መንፈስ ቅዱስ ወንድና ሴቶች ልጆችን፣ ሽማግሌዎችንና ወጣቶችን፣ ወንድና ሴት ባሪያዎችንም እንዲተነቢዩ እንደሚያደርጋቸው ነቢዩ ኢዮኤል አስቀድሞ ተናግሮ ነበር (ኢዮ 2:28-29)።

የጳውሎስ ግብረ አበሮች

"ጢሞቴዎስ ልጄ ሆይ፥ አስቀድሞ ስለ አንተ እንደ ተነገረው ትንቢት፥ በእርሱ መልካም ጦርነት ትዋጋ ዘንድ ይህችን ትእዛዝ አደራ እሰጥሃለሁ፤" (1 ጢሞ 1:18)



ከሐዋርያትና ከነቢያት በተጨማሪ እንደ ሲላስና በርናባስ የትንቢት ሥጦታ የነበራቸው አንዳንድ የጳውሎስ ግበረ አበሮችም ተጠቅሰው ነበር:

ጢሞቴዎስ



የአገልግሎት ጥሪው ተተንብዮ ነበር (1 ጢሞ 1:18)። በ 2ኛ ቆሮንቶስ (2 ቆሮ 1:1)፣ ፊልጵስዩስ (ፊል 1:1)፣ ቆላስይስ (ቆላ 1:1)፣ 1ኛ ተሰሎንቄ (1 ተሰ 1:1)፣ 2ኛ ተሰሎንቄ (2 ተሰ 1:1) እና ፊልሞና (ፊል 1:1) መልዕክቶች ላይ ተሳትፎ ነበር።

ቲቶ



ከትንቢታዊ አገልግሎቶች መካከል በሆኑት በማነጽ (2 ቆሮ 8:6)፣ በተግሳጽ (ቲቶ 2:6፣ 9፣ 15)፣ እና በማጽናናት (2 ቆሮ 7:13) ሲያገለግል ነበር።



ሀሰተኛ ነቢያት

"ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና።" (1 ዮሐንስ 4:1)




ኢየሱስ በ"ነጣቂ ተኩላዎች" የመሰላቸው ሀሰተኛ ነቢያት ወደፊት እንደሚነሱ አስጠንቅቆ ነበር (ማቴ 24:24፣ 7:15)። እነዚህ ሀሰተኛ ነቢያት በጥንቷ ቤተክርስቲያን ብቅ ማለት ጀምረው ነበር (1 ዮሐ 4:1)።

ጳውሎስ የኤፌሶን ሽማግሌዎችን "ጨካኝ ተኩላዎች" በመካከላቸው እንደሚነሱ አስጠንቋቸው ነበር (የሐዋ 20:29)። "ሀሰተኛ ሐዋርያትም" እንደሚኖሩ የቆሮንቶስ ሰዎችን አስጠንቅቆ ነበር (2 ቆሮ 11:13)።



እውነተኛ ትንቢት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የተስማማ፣ ወደ ክርስቶስ የሚጠቁም እና ቤተክርስቲያንን የሚገነባ ሲሆን ሀሰተኛ ነቢያት የሚከፋፍሉ ትምህርቶችንና የግል ጥቅማቸውን የሚያራምዱ ናቸው።



የእኛ የአማኞች ጥሪ ነቢያትን እንድንመረምር እና መልዕክቶቻቸው መጽሐፍ ቅዱስን የማይጣረስና ክርስቶስን ማዕከሉ ያደረገ መሆኑን እንድናረጋግጥ ነው።

ከሀሰተኛ ነቢያትና ከሚመሯቸው የጨለማ ኃይላት እራሳችንን የምንጠብቅበት ብቸኛ መንገድ እግዚአብሔር ያዘጋጀልንን ዕቃ ጦር መልበስ ነው (ኤፌ 6:10-18)።

“አበው፣ ነቢያት እና ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ እየተነዱ ተናገሩ፣ ይህም በራሳቸው ኃይልና ስም እንዳልሆነ በግልጽ ተናግረዋል። እነርሱ ምንም አይነት ድርሻ እንደነበራቸው ተደርጎ እንዳይወሰድና እነርሱ ባላመነጩት ነገር የሚመኩበት አንዳች እንዳላቸው ማንም እንዳያስብ ይመኙ ነበር። ምስጋና ሁሉ ስለሚገባው ለእግዚአብሔር ክብር ይቀኑ ነበር። የተሰጣቸው ኃይልና የተቀበሉት መልዕክት የእግዚአብሔር ኃይልን ለመወከል የተሰጣቸው አደራ መሆኑን አውጀው ነበር። እግዚአብሔር አዛዣቸውና ብቃታቸው ነበር።”

EGW (To Be Like Jesus, July 30)

አባሪ: የኤለን ጂ ኋይት አገልግሎት ቁልፍ መርሆዎች

የኤለን ጂ ኋይት አገልግሎት ሁለት መሰረታዊ ትኩረቶች የነበሩት ሲሆን እነርሱም ሕዝቡን ወደ ኢየሱስ ማምጣት እና ትኩረታቸውን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መምራት ነበር።



የመጀመሪያው ትኩረት: ኢየሱስ

ከ1888ቱ ስብሰባ በኋላ በቀረቡት ርዕሶች ጉዳይ ስትጠየቅ "ይህን ላለፉት 45 ዓመታት ሳቀርብላችሁ ነበር—እርሱም ወደር የሌለው የክርስቶስ ውበት ነው" ብላ ተናግራ ነበር (ስብከቶች እና ንግግሮች ቅጽ. 1, ገጽ 116)።





ሁለተኛው ትኩረት: መጽሐፍ ቅዱስ

ኤለን ጽሁፎችዋን በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲፈተኑ አሳስባለች እንጂ መቼም ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደሚበልጡ አድርጋ አቅርባ አታውቅም። እንደ ጌታ መልዕክተኛ "ታላቁ ብርሃን"ወደ ሆነው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ሕዝቡን የምትመራ "ታናሽ ብርሃን" አድርጋ እራሷን ትቆጥር ነበር (የተመረጡ መልዕክቶች, ቅጽ. 3, ገጽ 29)።

